Government of Saskatchewan

Saskatchewan Canada Immigration

እንግሊዝኛ ቋንቋ መማር

ጥ:- እንግሊዝኛ ቋንቋ መማር ለምን ይጠቅማል?

እንግሊዝኛ ቋንቋ በSaskatchewan የሚነገር ዋነኛ ቋንቋ ነው። ከዶክተርዎት፣ ከስራ አለቃዎት፣ ከጎረቤትዎት ጋር እና በንግድ መደብሮችም የሚነጋገሩት በእንግሊዝኛ ቋንቋ ነው። በየትኛውም የSaskatchewan ክልል ውስጥ ሰዎች የሚነጋገሩት በእንግሊዝኛ ቋንቋ ነው።እርስዎ Saskatchewan ውስጥ የሚኖርዎት የስኬት መጠን እንግሊዝኛ ቋንቋ መረዳትና መናገር ሲጀምሩ ይሻሻላል።

ካናዳ ውስጥ፣ በርካታ የቋንቋ ፕሮግራሞች “የካናዳ የቋንቋ ቤንችማርኮች” (Canadian Language Benchmarks) (ወይም ሲኤልቢ ተብሎ የሚጠራ - CLB) ሲስተም በመጠቀም እርስዎ የእንግሊዝኛ ቋንቋን በምን ያህል መጠን እንደሚናገሩ እና እንደሚረዱ ለመግለጽ እና ለመመዘን ይችላሉ። 12 የምዘና መስፈርቶች ያሉ ሲሆን 12 ከፍተኛው (የላቀ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ክህሎት) እና 1 ደግሞ ዝቅተኛው ነው። ብዙ ስራዎችን በጥሩ ሁኔታ ለማከናዎን፣ ቢያንስ 4 ቤንችማርክን ማሳካት ያስፈልጋል። አነስተኛ ቤንችማርክ ያለው ሰው ከሌሎች ጋር ሊሰራ እና ሊያወራ ይችላል። ነገር ግን ቢያንስ 4ኛ ቤንችማርክ ላይ ሳይደርሱ ከስራ አለቃዎት ወይም ከስራ ባልደረቦችዎት ጋር መውራት፣ ወደ መደብር ወይም ወደ ባንክ መሄድ፣ ከልጆችዎት መምህራን ጋር ወይም ከዶክተር ጋር ማውራት አስቸጋሪ ይሆንብዎታል። ስለ CLBs ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የካናዳ የቋንቋ ቤንችማርኮች (Centre for Canadian Language Benchmarks) ድህረ-ገጽን መጎብኘት ወይም በኦን ላይን የሚሰጥ የራስ ምዘና ፈተናን መውሰድ ይችላሉ (on-line self assessment)።

ወደዚህ ቦታ ከመምጣትዎት በፊት የእንግሊዝኛ ቋንቋን መማሩ ሊስፈልግዎት ይችላል፤ ምክንያቱም ወደዚህ ሲመጡ እና የሰፈራ እንቅስቃሴዎትን ለመጀመር የእንግሊዝኛ ቋንቋን መረዳትና መናገር ያስፈልግዎታል።

<u>ፍንጭ</u>፡ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታዎትን ለማሻሻል አንዱ መንገድ የእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ ድህረ-ገጾችን መጎብኘት ነው። በኢንተርኔት ላይ "የእንግሊዝኛ ቋንቋን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ፣" (English as a Second Language) "የእንግሊዝኛ ቋንቋን ይማሩ" (Learn English) ወይም "የእንግሊዝኛ ቋንቋ ቃላት" (English Vocabulary) የሚሉ ቃላትን ጽፈው ያፈላልጉ።

ወደ Saskatchewan እንደመጡ፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታዎትን ማዳበር አስፈላጊ ነው።

ጥ:- እኔ በምኖርበት ማህበረሰብ ውስጥ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ክፍሎችን እንዴት ማግኘት እችላለሁ?

1. ወደ Saskatchewan ሲመጡ፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ለመማር ስላሉ ዕድሎች መረጃ ለማግኘት በአቅራቢያዎት ያለውን ክልላዊ የአዲስ መጤዎች ማስተናገጃ ክፍል (Regional Newcomer Gateway) ያነጋግሩ። አብዛኞቹ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርቶች የሚሰጡት ከክፍያ ነጻ ነው።

ክልላዊ የአዲስ መጤዎችማስተናገጃ ክፍሎች (Regional Newcomer Gateways) ወደ Saskatchewan የሚመጡ አዳዲስ ነዋሪዎችን የሚቀበሉ ማዕከላት ናቸው። በመላው ክፍለ ሃገር ውስጥ 11 የአዲስ መጤ ማስተናገጃ ማዕከላት አሉ። አድራሻቸውን ከአዲስ መጤ ማስተናገጃ ማዕከላት አገናኝ ካርታ ላይ ማግኘት ይችላሉ (Interactive Map) ። የተለያዩ ስሞች ቢኖራቸውም፣ ሁሉም የሚሰጡት አገልግሎት ግን ተመሳሳይ ነው።

የአዲስ መጤዎች ማስተናገጃ ማዕከላት ዝርዝር እና የሚገኙበት ቦታ ከዚህ በታች ቀርቧል፡

- ኤስቴቫን (Estevan) – Southeast Newcomer Services
- ሐምቦልድ (Humboldt) – Humboldt Regional Newcomer Centre
- ሊሎይድሚኒስትር (Lloydminster) – Lloydminster Regional Newcomer Gateway
- ሙዝ ጃው (Moose Jaw) – Moose Jaw Newcomer Welcome Centre
- ኖርዝ ባትልፎርድ (North Battleford) – Battlefords Immigration Resource Centre
- ሬጂና (Regina) – Newcomer Welcome Centre
- ፕሪንስ አልበርት (Prince Albert) – Regional Newcomer Centre
- ሳሳካቱን (Saskatoon) – Newcomer Information Centre
- ስዊፍት ከረንት (Swift Current) – Southwest Newcomer Welcome Centre
- ቲስዳሌ (Tisdale) – Northeast Newcomer Services
- ዮርክተን (Yorkton) – Yorkton Newcomer Welcome Centre

2. አገናኝ ካርታ (interactive map) መማሪያ ክፍሎቹ የት እንደሚገኙ ሊጠቁማችሁ ይችላል።
3. የእንግሊዝኛ ቋንቋ መዛኝዎት (የቋንቋ ምዘና የሚያደርግልዎት ሰው) በአቅራቢዎት ስለሚገኙ የቋንቋ ማስተማሪያ ቦታዎች መረጃ ሊሰጥዎት ይችላል።
4. የሕዝብ ቤተ መጻሕፍት (Public libraries) እና ክልላዊ ኮሌጆችም (Regional Colleges) እርስዎ በሚኖሩበት አካባቢ ያሉ የቋንቋ ማስተማሪያ ክፍሎችን በመለየት ረገድ እገዛ ሊያደርጉልዎት ይችላሉ።

ጥ:- የእንግሊዝኛ ቋንቋን ለመማር የምዘገባው ሂደቶች ምን ምን ናቸው?

1. የቋንቋ መዛኝ ያስፈልግዎታል

ምዘናውን ካለፉ፣ ክልላዊ የአዲስ መጤዎች ማስተናገጃ ክፍል ወይም በአካባቢዎ የሚገኝ ክልላዊ ኮሌጅ ለቋንቋ ፈተና ቀጠሮ እንዲይዙ ያግዝዎታል ። ይህ የቋንቋ ፈተና፣ ወይም የቋንቋ ምዘናው የእርስዎ ሲኤልቢ ደረጃ ምን እንደሆነ እና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታዎትን ለማሻሻል የሚረዱዎት የቋንቋ ትምህርት ክፍሎች የትኞቹ እንደሆኑ ይነግርዎታል። የቋንቋ ት/ቤቱም ለእርስዎ ተስማሚ በሆነ ክፍል እንዲመድብዎትና መምህርዎት እርስዎን በፍጥነት ለማስተማር የሚያስችል ትምህርትን እንዲያቅዱ ያግዛቸዋል። ይህን አገልግሎት በጠየቁ በሰባት ቀናት ውስጥ የቋንቋ ምዘና ማግኘት አለብዎት። እባክዎ የመዘግየት ሁኔታ ካጋጠመዎት (contact us) ያሳውቁን።

የቋንቋ ምዘና ካለብዎት፣ ከቋንቋ መዛኙ ጋር የሚገናኙ ሲሆን መዛኙም እርስዎ እንግሊዝኛ ቋንቋን ምን ያህል ማንበብ፣ መጻፍ፣ መረዳት እና መናገር እንደሚችሉ ለማዎቅ የተለያዩ አስቸጋሪ ተግባራትን እንዲሰሩ

ይሰጥዎታል። የምዘናው ሂደት ከ30 ደቂቃ እስከ አንድ ሰዓት ድረስ ሊወስድ ይችላል። የቆይታ ግዜው የሚወሰነው እርስዎ የእንግሊዝኛ ቋንቋን በምን ያህል ደረጃ በጥሩ ሁኔታ መናገርዎት ላይ ነው።

ምዘናው ሲጠናቀቅ፣ የምዘና ውጤት ሰነድ የሚሰጥዎት ሲሆን ሰነዱ የንባብ፣ የማድመጥ እና ንግግር ውጤትዎን የሚያሳይ ነው። በካርዱ ላይ ‹‹1›› ማለት በተጠቀሰው ክህሎት ረገድ ጀማሪ እንደሆኑ እንዲሁም ‹‹8›› ደግሞ በክህሎቱ ጠንካራ እንደሆኑ የሚያሳይ ነው። ይህን ሰነድ ማስቀመጥ እና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ለመማር በሚመዘገቡበት ወቅት ማሳየት ይኖርብዎታል።መዛኙም እርስዎ ከሚኖሩበት በቅርብ ርቀት ላይ ስለሚገኙ የተለያዩ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መማሪያ እድሎች ይነግርዎታል።በእነዚህ ቦታዎች መማር የሚፈልጉ ከሆነ ስልክ በመደወል ወይም በአካል ሄደው በመጎብኘት ስለፕሮግራሞቹ ማወቅ ይችላሉ።በተጨማሪም ለቅጥር አገልግሎት ለመመዝገብ የምዘና ውጤት ሰነድዎን ማቅረብ ይኖርብዎታል።

ወደ Saskatchewan ለሚመጡ አብዛኛዎቹ አዳዲስ መጤዎች የቋንቋ ምዘና ይሰጣል።ለቋንቋ ምዘና ብቁ መሆን አለመሆንዎን በማወቅ ረገድ የክልላዊ አዲስ መጤዎች ማስተናገጃ ማእከልዎት (Regional Newcomer Gateway) ወይም ክልላዊ ኮሌጅ (Regional College) ይረዳዎታል። በማስተናገጃ ማዕከሉ ወይም ክልላዊ ኮሌጁ ለቋንቋ ምዘና ቀጠሮ በሚይዙበት ወቅት ሰራተኞቹ የትኞቹን ሰነዶች ማቅርብ እንደሚኖርብዎት ይነግርዎታል።

ከቋንቋ ምዘናው ያገኟቸውን ውጤቶች ለሚከተሉት ጉዳዮች መጠቀም አይችሉም፡

- የስደተኝነት ማመልከቻዎ፡- የቋንቋ ምዘና አገልግሎት ለስደተኝነት ማመልከቻ ወይም ለዜግነት ማማልከቻዎ የሚጠቀሙበትን የቋንቋ ውጤቶች አይሰጥዎትም። ለስደተኝነት የሚያስፈልጉ የቋንቋ ቅድመ ሁኔታዎችን በተመለከተ ለበለጠ መረጃ ‹‹የቋንቋ ቅድመ ሁኔታዎች እንዴት ማሟላት እችላለሁ?›› (How can I meet the language requirements?) የሚለውን ክፍል ይመልከቱ።ለዜግነት የሚያስፈልጉ የቋንቋ ቅድመ ሁኔታዎችን በተመለከተ ለበለጠ መረጃ በሲአይሲ ድረ ገጽ ላይ ‹‹ለቋንቋ ቅድመ ሁኔታዎች የሚያስፈልጉ (Acceptable documents for language requirements) ተቀባይነት ያላቸው ሰነዶች›› የሚለውን ክፍል ይመልከቱ።
- ለድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ተቋማት ስለማመልከት- ይህ አገልግሎት እንደ ዩኒቨርስቲ ወይም ኤስአይኤኤስቲ ለመሳሰሉ ድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ተቋማት ለማመልከት አይረዳዎትም። በድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ተቋማት መማር የሚፈልጉ ከሆነ፣ ሊማሩበት ከፈለጉበት ተቋም ጋር ግንኙነት መፍጠር ይኖርብዎታል።

2. በሚሰጡበት ቦታ ካሉት የትምህርት ዓይነቶች መካከል ለእርስዎ ተስማሚ ነው የሚሉትን ይምረጡ።

የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት የሚሰጡ ብዙ ድርጅቶች አሉ።ኣሳታፊ ካርታ (interactive map) ድርጅቶቹ የት እንደሚገኙ ያሳያል።

ጥ:- ምን አይነት የቋንቋ ትምህርቶችን መውሰድ እችላለሁ?

በቋንቋ ምዘናው መጨረሻ ላይ በአካባቢዎ ስለሚገኙ የቋንቋ ትምህርት ስለሚሰጥባቸው መማሪያ ክፍሎች ይነገርዎታል።

ደረጃ 1(Stage 1) እንግሊዝኛ ተብለው የሚጠሩት አንዳንዶቹ የቋንቋ የትምህርት ክፍሎች ለጊዜዊም ሆነ ለቋሚ ነዋሪዎች ይቀርባሉ።ደረጃ 1 እንግሊዝኛ አዲስ መጤዎች የቀን ተቀን እንቅስቃሴዎችን

ለመከወን የሚረዳ መሰረታዊ እንዲሁም በስራ ላይ መዋል የሚችል እንግሊዝኛ ቋንቋ ክህሎት እንዲኖራቸው ደርጋል።ደረጃ 1 እንግሊዝኛ የተባለበት ምክንያት የቋንቋ ብቃት የመጀመሪያው ደረጃ በመሆኑ ነው።የሚሰጡት የቋንቋ ክፍሎች የሲ ኤል ቢ ደረጃዎች ከ1 እስከ 4 ናቸው።

ሌሎች LINC ተብለው የሚጠሩት ትምህርቶች (ወደ ካናዳ የመጡ አዲስ መጤዎች የቋንቋ መመሪያዎች) (Language Instruction for Newcomers to Canada) ለቋሚ ነዋሪዎች ብቻ የቀረቡ ናቸው።የቋንቋ ክፍሎቹ ተማሪዎችን እስከ ሲ ኤል ቢ 8 ቤንች ማርክ ድረስ ያግዛቸዋል።

ትምህርቶቹ በተለያዩ ጊዜያት እና በተለያዩ ቦታዎች ይሰጣሉ።እንደ ሬጂና (Regina) እና ሳስካቱን (Saskatoon) የመሳሰሉ ትልልቅ ከተማዎች ለመምረጥ የሚመቹ ብዙ የመማሪያ ክፍሎች አሉ።አንዳንዶቹ ትምህርቶች ጠዋት ላይ የሚሰጡ ሲሆን አንዳንዶቹ ደግሞ ከሰዓት በኋላ ወይም ምሽት ላይ ይሰጣሉ።በተጨማሪም የሙሉ ግዜ ወይም የትርፍ ሰዓት የትምህርት ዝግጅቶች ሊኖሩ ይችላሉ። አነስተኛ በሆኑ ከተሞች በአቅራቢያዎ የሚሰጥ የትምህርት ፕሮግራም ሊኖር የሚችል ሲሆን ወይም ደግሞ በግል አስጠኚ እርዳታ እንግሊዝኛ ቋንቋን ሊማሩ ይችላሉ።

አብዛኛዎቹ ትምህርቶች እርስዎ በሚኖሩበት ማህበረሰብ የቀን ተቀን ህይወት ውስጥ ሊገለገሉበት የሚያስችል እንግሊዝኛ እንዲማሩ ይረዱዎታል። ሌሎች የትምህርት ፕሮግራሞች ደግሞ ስራ ለመፈለግ እና ለስራ መዘጋጀት የሚያስችል እንግሊዝኛ እንዲማሩ ይረዱዎታል።

እነዚህ የትምህርት ፕሮግራሞች እርስዎን ወደ ዩኒቨርሲቲ እንዲገቡ ወይም የሙያ ፍቃድ እንዲያገኙ የሚያዘጋጁዎት አይደሉም። የሬጂና ዩኒቨርስቲ (University of Regina)፣ የSaskatchewan ዩኒቨርስቲ (University of Saskatchewan)፣ እና የSaskatchewan አፕላይድ የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ተቋም (ኤስአይኤኤስቲ - SIAST) (Saskatchewan Polytechnic) በድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ለመማር በሚገባ እንግሊዝኛ መማር ላለባቸው ሰዎች ከፍ ያለ ደረጃ ያላቸውን የትምህርት ፕሮግራሞች ሊሰጡ ይችላሉ።

ጥ:- የእንግሊዝኛ ቋንቋ በምን ያህል ቅርብ ጊዜ ውስጥ መጀመር እችላለሁ?

ደረጃ 1 እንግሊዝኛ ኤልአይኤንሲ ትምህርቶችን መውሰድ ከመጀመርዎት በፊት በSaskatchewan ነዋሪ መሆን አስፈላጊ ሲሆን በተጨማሪም የቋንቋ ምዘና ውጤት ሊኖርዎት ይገባል።

የደረጃ 1 እንግሊዝኛ ክፍሎች አብዛኛውን ጊዜ በየሁለት ሳምንቱ አዳዲስ ተማሪዎችን ይቀበላሉ። ኤልአይአንሲ ትምህርት ፕሮግራሞች አብዛኛውን ጊዜ በትምህርት ላይ ሆነውም ተማሪዎችን ይቀበላሉ።

የተወሰነ ጉዳይ ላይ የሚያተኩሩ ትምህርቶን ለመውሰድ የተመዘገቡ ሰዎች ወረፋ ሊኖር ይችላል። እባክዎ የእንግሊዝኛ ትምህርት ለመውሰድ ከአራት ሳምንት በላይ ጠብቀው ከሆነ (contact us) እኛን ያነጋግሩን እና ልንረዳዎት እንሞክራለን።

ጥ:- የእንግሊዝኛ ቋንቋ ኮርሶችን ለመማር ምን ያህል ገንዘብ ያስወጣል?

ደረጃ 1(Stage 1) እንግሊዝኛ ወይም ኤልአይኤንሲ (LINC) ትምህርቶችን ለመውሰድ **ክፍያ የለውም።**